የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

OF THE HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

8ኛ ዓመት ቁጥር 3
8th Year NO 3

ሐረር መጋቢት 1 ቀን 1996
HARAR 11th March,2004

የአንዱ ዋጋ
Unit price 1.00

በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

ፖስታ ሳጥን ቁጥር
p.o.Box 272

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 36/1996 ዓ.ም

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1988ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ-------------------------------------------------------------------ገጽ 312

## አዋጅ ቁጥር36/1996

## የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1988ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ።

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1988ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፡

በክልሉ መንግስት ህገ-መንግስት አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ /2//ሀ/መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1.አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1988ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 36/1996" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ማሻሻያ፤

የክልሉ መንግስት አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1988 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

1 የማቋቋሚያ አዋጁ ምዕራፍ አንድ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (5) ቀጥሎ የሚከተለው ንዑስ አንቀጽ (6) ተጨምሯል።

«6 «ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ» ማለት በክልሉ መንግስት ሕገ-መንግስት ከፍተኛ የአስፈጻሚነት ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው።»

2. ከማቋቋሚያ አዋጁ አንቀጽ 25 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ተጨምሯል።

"26 ደንብ የማውጣት ሥልጣን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም አስፈላጊውን ደንብ የማውጣት ሥልጣን ይኖረዋል።››

3. የማቋቋሚያ አዋጅ አንቅጽ 26 እና 27 እንደቅደም ተከተላቸው አንቅጽ 27 እና 28 ሆነዋል።

3. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ማሻሻያ አዋጅ ከመጋቢት1 ቀን 1996 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐረር መጋቢት1 ቀን 1996ዓ/ም

ፉአድ ኢብራሂም

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዝዳንት